# የእስክንድር ነጋን መንገድ እደግፋለሁ!!

አርቲስት ሽመልስ አበራ

ይህን ማድረግ ደግሞ መብቴ ነው!፡፡ ለምሳሌ ሌላ ቦታ ተቃውሞና ሰልፍ ማድረግ እየተፈቀደ አዲስ አበባ ይከለከላል፡፡ ለምን ?
መንግስት እያለ ማንም ወጥቶ ድንጋይ እየኮለኮለ መንገድ ሲዘጋ ዝም ይባላል፡፡ ሱዳን እኮ ዳቦ ላይ 10 ሳንቲም ተጨመረ ተብሎ ነው ሰዉ ሰልፍ የወጣውና መንግስትን ያስወገደው፡፡ እዚህ ሰላም አጥተህ እየኖርክና በኑሮ እየተሰቃየህ መቃወም አትችልም ትባላለህ፡፡ ችግሩ መቼ ነው የሚፈታው ስትል ሀገር የሚገዙትም ዝምታ ነው መልሳቸው፡፡
ይህ ዝምታ እስከመቼ ነው የሚቀጥለው ብዬ ነው የምቃወመው፡፡ ዛሬ ላይ ስልጣኑ ከላይ እስከ ወረዳ የተያዘው በአንድ ቡድን ነው፡፡ ባንኩም ሆነ ሌላው የተያዘው በአንድ ወገን ነው፡፡ ትምህርቱ፡ እውቀቱና ብቃቱ እስካለው ድረስ የፈለገውን ያክል ጊዜ ማንም ቢገዛ በግሌ ቅሬታ የለኝም፡፡

